# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 109 ሰኔ 10 ቀን 2002 ገጽ 1

### የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!፡”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ወደ ካናዳ የሚያደርገው ጉዞ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው

ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ በቡድን 20 ወይም ጂ20 ስብሰባ ለመሳተፍ ወደ ካናዳ የሚያደርገው ጉዞ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል።

በካናዳ የሚገኙ ሶማሊዎች ማህበር የሆነው “ካኔዲያን ሶማሊ ኮንግረስ” በዚህ ሳምንት ባወጣው መግለጫ ካናዳ መለስ ዜናዊን ለስብሰባው በመጋበዟ ማዘኑን ገልጿል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያውያን እና በሶማሊዎች ላይ የሰብአዊ መብት ረገጣን የሚያደርግ፤ ዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የሚጨቁን፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ በጥብቅ የሚገታ፤ የተቃዋሚ አባላትን የምግብ እርዳታ የሚከለክል፤ እንዲሁም በሶማሊያ የተባበሩት መንግስታትን የጦር መሳሪያ ማእቀብ በመጣስ የተለያዩ ቡድኖችን የሚያስታጥቅ ነው ብሏል።

ማህበሩ ካናዳዊ ዜጋ የሆነውን እና በወያኔ ፍርድ ቤቶች የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደበትን የባሺር ማክታልን እስርም ተቃውሟል። ባሺር ማክታል በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ካናዳዊ ዜጋ ሲሆን፤ ከሶስት አመታት በፊት የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር አባል ነው በሚል በወያኔ ታስሮ የሰቆቃ ማስፈራሪያ እንደደረሰበት እና የውሸት ኑዛዜ ለማድረግ መገደዱ ከዚህ ቀደም ተዘግቧል። በካናዳ የሚገኙት የባሺር ቤተሰቦችም የዘረኛውን አምባገነን የካናዳ ጉዞ ከሚቃወሙት ውስጥ ሲሆኑ፤ የካናዳ መንግስት ለመለስ ዜናዊ ያደረገውን ግብዣ እንዲሰርዝ ጥሪ አድርገዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## መድረክ ፓርቲ የምርጫ ቦርድን ውሳኔ በመቃወም ወደ ፍርድ ቤት ሄደ

የወያኔ ምርጫ ቦርድ የድጋሚ ምርጫ አይካሄድም በማለት ያስተላለፈውን ውሳኔ በመቃወም መድረክ ፓርቲ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረቡ ታወቀ።

የፓርቲው ሊቀመንበር ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ለሬውተርስ የዜና አገልግሎት በሰጡት ቃል፤ 87 ገጽ ያለው የማስረጃ ሰነድ ለምርጫ ቦርድ ቢያቀርቡም፣ አንድም ማብራሪያ ወይም ምስክሮች እንዲያቀርቡ ሳይጠየቁ ቦርዱ ውሳኔውን ማስተላለፉን ገልጸዋል። የምርጫ ቦርድ እንደሌሎች የመንግስት ተቋማት ሁሉ ሙሉ በሙሉ በወያኔ ቁጥጥር ስር እንዳለ ይታወቃል።

በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት እለትም በአንዳንድ አካባቢዎች የቦርዱ ስራ አስፈፃሚዎች ወያኔን ምረጡ ብለው በግልጽ እስከመቀስቀስ ድረስ ለገዢው ፓርቲ ሲሰሩ እንደነበር ተዘግቧል። በተለይ ከሳምንት በፊት ዘግይቶ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ እንደሚያሳየው፥ በባህር ዳር ከተማ አንዳንድ አካባቢዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ከምርጫ ቦርድ የተቀበሉ የወያኔ አባላት ምርጫ ከመካሄዱ በፊት ከግንቦት 8 – 11 ቀን ከቤት ቤት በመዞር ነዋሪዎች ሰላምና ልማት ከፈለጉ ከንብ ምስል ጎን ምልክት በማድረግ እንዲመርጡ ሲያደርጓቸው እንደበር ለማወቅ ተችሏል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በኋላ በዜጎች ላይ የበቀል እርምጃ እየወሰደ መሆኑ ታወቀ

የምርጫ ተውኔቱ ከመካሄዱ በፊት ማስፈራራት ሲደርስባቸው በነበሩ ዜጎች ላይ የአገዛዙ ሎሌዎች የበቀል ጥቃት መፈጸም መጀመራቸውን ዘገባዎች እያሳዩ ነው።

ኢትዮሚድያ በሚባለው የዜና ድረ-ገጽ ላይ ሰሞኑን እየወጡ ያሉ ተከታታይ ዘገባዎች እንደሚያስረዱት፤ በተለይም በደቡብ ክልል በዜጎች ላይ በሰፊው ጥቃት እየደረሰ ነው። የምርጫ ታዛቢዎች በሃሰት እየተወነጀሉ እና ክስ ሳይመሰረትባቸው ለረዥም ቀናት ታስረው እንዲቆዩ እየተደረገ እንደሆነ ታውቋል።

በጋሞ ጎፋ ዞን በደረማሎ ወረዳ በመስቃ ቀበሌ በድምጽ መስጫ እለት ሶቻ ሶራቶ የተባለ የቀበሌው መሬት አስተዳደር ሃላፊ የሆነ ካድሬ ድምጽ በሚሰጥበት ስፍራ ላይ ተቀምጦ እያንዳንዱ መራጭ ማንን እንደመረጠ ሲቆጣጠር እና ሲመዘግብ እንደዋለ፤ በዛም መሰረት ወያኔን አልመረጡም የተባሉ ሁለት ዜጎች መኖሪያ ቤቶች በድንጋይ መደብደባቸው በዘገባዎቹ ተገልጿል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጭት እንደገና ተቋረጠ፤ የወያኔ አገዛዝ ለአፈናው ተጠያቂ ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ወይም ኢሳትን አፍኗል ተባለ። ኢሳት ቅዳሜ እለት ባስተላለፈው ዘገባ፣ የጣቢያው ማኔጅመንት የወያኔ አገዛዝ የቴሌቭዥን ድርጅቱን ስለማፈኑ ማስረጃ ለማሰባሰብ ችሏል ብሏል።

የሳተላይት አገልግሎት አቅራቢ ኩባንያው በበኩሉ የአፈናውን ምንጭ ለመረዳት ምርመራውን እንደቀጠለ እና በቂ ማስረጃ ሲያገኝም ህጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ መግለጹን የኢሳት መግለጫዎች አሳይተዋል።

ዘረኛው አገዛዝ ከዚህ ቀደም ሌላ ኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎችን እንደሚያፍን እራሱ ማመኑ ይታወቃል። መለስ ዜናዊ ኢሳት ቴሌቪዥንን እንዴት ማቆም በሚችልበት መንገድ ላይ ለመምከርም ከሳምንታት በፊት በቢሮው አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ እንደነበር ከዚህ ቀደም መዘገቡም ይታወሳል።

በጉዳዩ ላይ ያነጋገርናቸው ግለሰቦች የሳተላይት ስርጭት ለማፈን የሚያስችለው ቴክኖሎጂ እና በስራም ላይ ለማዋል የሚያስፈልገው ወጪ በጣም ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ በመሆኑ የወያኔ አገዛዝ ይህንን በራሱ ለማድረግ ይችላል ብለው እንዳልገመቱ ገልጸዋል። በርግጥም አገዛዙ አፈናውን እራሱ እያደረገው መሆኑ ከተረጋገጠ እኩይ ተግባራትን ለመፈጸም ሲል በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እየተራቡ የህዝብን ገንዘብ በገፍ ከማፍሰስ ወደ ኋላ እንደማይል ያሳያል ብለዋል። አፈናውን የሚያስፈጽመው በሶስተኛ አገር አማካኝነትም ቢሆን፣ ወያኔ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ ለማፍሰስ እንደሚገደድ ግምታቸውን ገልጸዋል።

ሌሎች ምንጮች የሳተላይት አፈና ለማካሄድ ቢያንስ ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌክትሪክ ሃይል እንደሚያስፈልግ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በኦጋዴን ንጹሃን ዜጎችን እየገደለ መሆኑ ተዘገበ

የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) የወያኔ አገዛዝ ባለፈው ወር ብቻ በኦጋዴን 71 ንጹሃን ዜጎችን መግደሉን ለዜና አውታሮች በላከው መግለጫ አስታውቋል።

ግንባሩ በመግለጫው፥ ወንዶች ቤተሰቦቻቸው ፊት ሲገደሉ፤ ሴቶች ተደብድበዋል፣ ተደፍረዋል፣ ተገድለውማል ማለቱን ሬውተርስ የዜና አውታር ዘግቧል። ጉዳዩን አስመልክቶ የተጠየቀው የበረከት ስምኦን ምክትል ሽመልስ ከማል አገዛዙ ጉዳዩን እየመረመረ እንደሚገኝ እና እስካሁን የተደረገው ምርመራ መሰረተ ቢስ እና ውሸት መሆኑን፤ እንዲሁም በአካባቢው እየተካሄደ ያለ ውጊያ የለም ብሏል።

ኦብነግ በመግለጫው የጠቀሰው ስለ ሲቪሊያኖች ኢ-ፍትሃዊ ግድያ ሆኖ ሳለ ሽመልስ ከማል ስለ ጦርነት አለመኖር መናገሩ ግልጽ አይደለም። ይሁን እንጂ በአካባቢው በኦብነግ እና በወያኔ መካከል በየጊዜው ውጊያ እንደሚካሄድ ዘገባዎች ያሳያሉ። እስካሁን የሚሰጠው የአገዛዙ ምላሽም የተዘበራረቀ ሆኖ ቆይቷል። አንዳንዴ ኦብነግ ከስፍራው ተጠራርጎ መውጣቱን የሚናገሩት የአገዛዙ ቃለ አቀባዮች፤ በሌላ ጊዜዎች ደግሞ ውጊያ መፈጸሙን ሳይክዱ አገዛዙ ማሸነፉን ሲናገሩ ተደምጠዋል።

በኦጋዴን በንጹሃን ላይ የሚደረግ ግድያን በተመለከተ ከዚህ ቀደም ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ቡድን በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለው የኢትዮጵያ ጦር የጦር ወንጀል እና በሰብአዊነት ላይ የሚደረግ ወንጀል መፈጸሙን መግለጹ ይታወሳል። በወቅቱ አገዛዙ በኦጋዴን ወንጀል መፈጸሙን በተደጋጋሚ ቢክድም፤ “አሜሪካን አሶሲየሽን ፎር ዘ አድቫንስመንት ኦፍ ሳይንስ” የተባለው ድርጅት በሳተላየት የተወሰዱ የተቃጠሉ የኦጋዴን መንደሮች ፎቶግራፎችን ማውጣቱ ይታወሳል።

## ምርጥ የእግር ኳስ ተጫዋቾች እና ምርጥ ቡድኖች እንዲኖሩን መንገድ እናመቻች፤ እንቅፋቶችን እናስወግድ!!!

በደቡብ አፍሪቃ በመካሄድ ላይ ያለው የዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ በአገራችን የእግር ኳስ መሠረታዊ ችግሮች ላይ እንድናተኩር እድል ሰጥቶናል። ኢትዮጵያ በወጣቶች የተገነባች እና ከፍተኛ የሆነ የእግር ኳስ ፍቅር ያለባት አገር ናት። በትላልቅ የእግር ኳስ ሜዳዎችና ግጥሚያዎች ኢትዮጵያዊያንንና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለማየት ግን አልታደልንም። አገራችን እንኳንስ በዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ ልትወዳደር ቀርቶ ራሷ ካስጀመረችው የአፍሪካ እግር ኳስ ዋንጫ እንኳን ከተባረረች ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ሆኗል።

ከጥቂት ወራት በፊት በአንድ ፕሮግራም ላይ የቀረበ ኢትዮጵያዊ ታዳጊ ህፃን ሲያድግ መሆን ስለሚመኘው ነገር ሲጠየቅ "ኤምሬት ስታድየም ውስጥ ገብቼ የአርሴናልን ጨዋታ መመልከት" ሲል መልሷል። የታዳጊው ምኞት ምርጥ ተጫዋች ወይም ምርጥ አሰልጣኝ፤ አሊያም የምርጥ ክለብ ወይም የምርጥ ስታዲየም ባለቤት መሆን ሲገባው የልጅነት ምኞቱን እሚያደንቀው ስታድየም ውስጥ ገብቶ መመልከት በመቻል ላይ መገደቡ ከምን የመጣ ነው? ይህ አንድ ተራ አጋጣሚ አይደለም። ሰሞኑን የተደረገ አንድ አነስተኛ ጥናት "በእርስዎ ግምት ኢትዮጵያ መቼ ለዓለም እግር ኳስ ዋንጫ ትሰለፋለች?" ሲል ጠይቆ በተለያዩ የእድሜ ክልሎች ከሚገኙ የአዲስ አበባና አካባቢው ነዋሪዎች ያገኘውን ምላሽ ለአስተዋለ ሰው ከታዳጊው ህፃን ምኞት የበለጠ አስደንጋጭ ነው። ወደ ሃያ በመቶ የሚጠጉት ምላሽ ሰጪዎች "ኢትዮጵያ ለዓለም ዋንጫ ግጥሚያ እስከመቼውም አትደርስም" ሲሉ፤ ስድሳ በመቶ የሚሆኑት ደግሞ "ከሃያ ዓመት በላይ ይወስድባታል" ብለዋል። ይህ ተስፋ መቁረጥ ከምን የመጣ ነው? እየትስ ያደርሰናል?

በእግር ኳስ ፍቅር ብራዚልን እናስንቅ ይሆናል። ኢትዮጵያዊያን ታዳጊዎችና ወጣቶች ስለ ዓለም ምርጥ ተጫዋቾችና አሰልጣኞች ያላቸው የጠለቀ እውቀት ይገርማል። በዓለም የታወቁ ተጫዋቾችና አሰልጣኞች የሚሰሯቸውን ጥቃቅን ስህተቶችን ነቅሰው ማውጣት የሚችሉ በርካታ ተመልካቾች አሉን። ነገር ግን ለእግር ኳስ ያላቸው ፍቅር እና እውቀት የቱን ያህል የጠለቀ ቢሆን ከተመልካቾችነትና አድናቂነት ማለፍ አልቻሉም። በስሜትና እውቀት ደረጃ ያላቸውን አንድ ሺህኛ ያህል እንኳን በተግባር ላይ ማዋል አልቻሉም። በጣም የሚያስደነግጠው እነዚህ ወጣቶች ዛሬ የበቁ ተጫዋቾችና አሰልጣኞች አለመሆናቸው ብቻ አይደለም፤ ለነገም የበቃ ተጫዋቾችና አሰልጣኝ በኢትዮጵያ ምድር ሊበቅል ይችላል ብለው ተስፋ የማያደርጉ መሆኑን ነው። ይህ ነው ትልቁ የሀሊና ስብራት።

የእግር ኳስ ጥማታችን እና እግር ኳሳችን ያሉበት የሰማይና ምድር ያህል የተራራቀ ሁኔታ መላውን ኑሮዓችንን ገላጭ ነው። በእግር ኳስ የምናየው በሌላውም የኑሮዓችን ዘርፍ ያለ ነው። ልክ እንደ እግር ኳሱ ሁሉ የፍትህ ጥማታችን እና የፍትህ ሥርዓታችን፤ የአንድነት ጥማታችን እና አንድነታችን፤ የዲሞክራሲ ጥማታችን እና ዲሞክራሲያችን የሰማይና የምድር ያህል ተራርቀዋል። ወጣቱ እግር ኳስን ይወዳል፤ እግር ኳስን ያውቃል ነገር ግን እግር ኳስ አይጫወትም። ሕዝባችን ዲሞክራሲን ይወዳል፤ ዲሞክራሲን ያውቃል ነገር ግን በዲሞክራሲ አይተዳደርም። ሕዝባችን ፍትህን ይሻል፤ ፍትህን ያውቃል ነገር ግን ፍትህ አያገኝም። ሌላውም ሁሉ እንደዚያው ነው።

አምባገነኖች በረሃብና ጥማታችን እንደተጫወቱብን ነው። በቴሌቪዥንና ራድዮ ስለተትረፈረፈ ምርት እያወሩ እንደሚያስጎመጁን ሁሉ እግር ኳስንም በወሬና ምስል ብቻ ያንበሻብሹናል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሬድዮዎች ሁሉ ቀኑን ሙሉ አንድን ጨዋታ ሲተነትኑ ይውላሉ። አሁን የዓለም ዋንጫ ሰሞን ስለሆነ አይደለም ድሮም እንደዚያው ነበሩ፤ ሁሌም እንደዚያ ናቸው። ከሕዝብ በተሰበሰበ ታክስ የሚተዳደሩት ሚዲያዎ ስለ እንግሊዝ ፕሪመር የስንት ሰዓታት ትንተና ሰጥተዋል? የዚህን ስንት ስንተኛ የራሳችንን ቡድኖች ለማጠናከር ዋለ? የዚህን ስንት ስንተኛ ሌሎች አንገብጋቢ ችግሮቻችንን ለመወያየት ዋለ? ስለ እግር ኳስ፤ ስለዲሞክራሲ እና ስለህግ የበላይነት በመደስኮር ወያኔን የሚህል የለም፤ ተግባሩ ላይ ግን ፈጽሞ የለም።

እኛ ምን ያንሰናል? ከወጣቶቻችን መካከል ምርጥ ተጫዋቾችን ማፍራት አንችልም? በምርጥ ተጫዋቾች የተገነቡ የስፖርት ክበባትንስ መፍጠር አንችልም? የእግር ኳስ ተመልካች ብቻ ሆነን የቀረነው ወጣቱን በሙያና ክህሎቶች ለማነጽ የሚተጋ መንግሥት እና ለዚህም የተመቸ ሥርዓት የሌሉን በመሆኑ ነው። ስንት መጫወቻ ሜዳዎች አሉን? ወጣቶች የሠፈር ክለብ እንኳ ሲያቋቁሙ ወያኔ ካልገባበት አይሆንም። ነፃ የስፖርት ክበባት የሉንም። የነፃ ተቋማት አለመኖር የፖለቲካ ምርጫዎቻችንን እንዳዋረዱ ሁሉ የነፃ የስፖርት ተቋማት አለመኖር እግር ኳሳችንን አሽመድምደው።

ልክ እንደምርጫ፣ ልክ እንደ ፍርድ ቤት እግር ኳስም ማጭበርበሪያ ሲሆን ማየት በእጅጉ ያሳዝናል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመስቀል አደባባይ ሰልፍ ለመጥራት በጠየቁ ጊዜ የተሰጣቸው መልስ "ለፀጥታ አስጊ ነው" የሚል ነበር። የኢትዮጵያ ወጣቶች እንኳንስ በሰልፍ በኳስ እንኳን ሳይጣሉ መስቀል አደባባይ አምሽተው በሰላም ይመለሳሉ። ለተቃውሞ ሰልፍ የተከለከለ አደባባይ ለኳስ መመልከቻነት መፈቀዱ በራሱ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድነው?

እንደሚታወቀው እግር ኳስ ከጨዋታነቱ በላይ ብሄራዊ ስሜትን መግለጫ፤ በሕዝቦች መካከል መቀራረብን ማጎልበቻ ሆኗል። እኛ አድናቂዎች ብቻ ሆነን ስንቀር የሚጎዳው ብሄራዊ ማንነታችንም ጭምር እንጂ የስፖርት ስሜታችን ብቻ አይደለም።

ዛሬም አምርረን ከተነሳን አገራችን ከአለም የእግር ኳስ ዋንጫ ተፎካካሪ አገሮች ተርታ የማትገባበት ምክንያት የለም። አገራችን በዚህ ቀደምም አቶ ይድነቃቸው ተሰማን የመሰሉ የእግር ኳስ ጠቢብ አፍርታለች። ጋሬጣው ተጠርጎ ሥርዓት ከተበጀ የወጣቶች አገር የሆነችው ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዓለም ዓቀፍ ዝና ያላቸው የእግር ኳስ ተጫዋቾችንና ባለሙያዎችን ማፍራት የሚቸግራት አይሆንም። ለዚህ ሁሉ ጥርጊያ መንገዱ አድናቂዎች ብቻ እንድንሆን ያደረገንን፤ የማደግ ተስፋችንን ያጨለመብንን ወያኔን ማስወገድ ነው።

እንደፖለቲካና ኢኮኖሚያችን ሁሉ ወያኔ እግር ኳስንም በቴሌቪዥንና በወሬ ሊያጠግበን ይፈልጋል። እኛ ግን ከዛ በላይ እንፈልጋለን። እኛም ተጫዋቾችና አሰልጣኞች መሆን እንፈልጋለን እንላለን። ወያኔን አስወግደን ዓለምንበት እንደርሳለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ወደ ካናዳ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

"ማርች ፎር ፍሪደም" የሚባለው ቡድን እና ሌሎች በካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ማህበራት እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ጁን 26 በቶሮንቶ ከተማ የዘረኛውን አምባገነን መገኘት በመቃወም ሰልፍ እንደሚያደርጉ ከዚህ ቀደም ተዘግቧል። በተያያዘ ዜና በአሜሪካ ዋና ከተማ ዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የግንቦት 15ቱን የምርጫ ተውኔት በመቃወም ሰልፍ አድርገዋል። ሰልፈኞቹ የአሜሪካ መንግስት ከወያኔው አገዛዝ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲመረምር ጥሪ አቅርበዋል።

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ከግንቦት 15ቱ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚህም በተጨማሪ በሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ ድብደባ እና መፈናቀል እየደረሰ ያለ ሲሆን፤ የአንዳንዶቹ መኖሪያ ቤቶች እና እርሻዎች ላይ ጥቃት በማድረስ ንብረታቸው እንዲወድም እንደተደረገም ታውቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በደቡብ ክልል የጋሙ ጎፋ ዞን ነዋሪዎች በሆኑ ዜጎች የተፃፉ አቤቱታዎች ወጥተዋል። አንዳንድ አቤቱታ አቅራቢዎች ከግንቦት 15 በፊት ማስፈራሪያ እንደደረሰባቸው እና ከመኖሪያ ቤቶቻቸው እንዳይባረሩ ወይም እርዳታ እንዳይከለከሉ በመፍራት ወያኔን ለመምረጥ መገደዳቸውን አስፍረዋል። ሌሎቹ ደግሞ በድምጽ መስጫው እለት ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ማን ማንን እንደመረጠ ሲከታተሉ በነበሩ ካድሬዎች ወያኔን አለመምረጣቸው በመረጋገጡ በመኖሪያ ቤቶቻቸው ላይ ጥቃት መድረሱን ገልጸዋል።

### በኢትዮጵያ ላለው ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት የወያኔ የገንዘብ ፖሊሲ ተጠያቂ ነው ተባለ

በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ለባሰ ድህነት የዳረገው የዋጋ ግሽበት ወያኔ እንደሚለው እድገት የፈጠረው ሳይሆን በአገዛዙ የገንዘብ ፖሊሲ ምክንያት የተፈጠረ ነው ተባለ።

ባለፉት አራት አመታት በኢትዮጵያ ከቁጥጥር ውጪ በወጣ መልኩ ከሚታየው የዋጋ ግሽበት የተነሳ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት እያቃታቸው የኑሮ ደረጃቸው ወደከፋ ደረጃ ማሽቆልቆሉ እና ቁጥራቸው የማይታወቅ የከተማ ነዋሪዎች የሚበሉትን እስከማጣት መድረሳቸው ይታወቃል። ይህንን በሚመለከት የወያኔ አገዛዝ እድገት ያመጣው የዋጋ ግሽበት እያለ ለማምታታት የታሰቡ የፕሮፓጋንዳ መልክቶችን ለህዝቡ ሲያስተላልፍ ቆይቷል።

አገዛዙ በአገሪቱ ስም ከውጭ የተበደረው ገንዘብ መጠን 65.9 ቢሊዮን ብር መድረሱን እና፤ ባለፈው አንድ አመት ከግማሽ ብቻ 39 ቢሊዮን ብር መበደሩን፤ ያም እስከዛ ባሉት አመታት በተበደረው መጠን ላይ የመቶ አርባ አራት ፐርሰንት ጭማሪ መሆኑን ሰሞኑን ዘግበናል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በ1997 የህዝብ ድምጽ ከሰረቀ በኋላ የህዝቡን እና የአለማቀፍ ማህበረሰቡን ትኩረት ከፖለቲካው ሁኔታ ላይ ለማንሳት፤ እንዲሁም ለገዢው ፓርቲ አባላትን ለማጋበስ ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች በገበያው ላይ አገሪቱ የሌላትን ገንዘብ ማፍሰሱ ይታወሳል። ከውጭ አገር ከተበደረው ገንዘብ በተጨማሪ ከአገር ውስጥ ባንኮች በህግ ከተደነገገው መጠን በላይ መበደሩም ይታወቃል። አገዛዙ ያለበት የአገር ውስጥ እዳ ከአገሪቷ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ሰላሳ በመቶ በላይ እንደሚሆን የሲ.አይ.ኤ የአገራት መረጃ ድረ-ገጽ ይገልጻል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪያ

**(ይህ መግለጫ ባለፈው ዓመት በ2001 ዓ.ም በነሐሴ ወር የወጣ ሲሆን ከምርጫ ጋር በተያያዘ ያለፍንበትንን፣ የአሁኑን የወደፊቱንም በጥልቀት የዳሰሰ በመሆኑ በድጋሚ እንዲነበብ እንጋብዛለን) (ክፍል 1)**

### 1. መግቢያ

ወያኔ ምርጫ 2002ን በተመለከተ የመራጬንና የተወዳዳሪውን ገደብ፤ የሚያመቸውን ጊዜና የምርጫ ዳኛውን በዚያውም የምርጫውን ውጤት ነድፎ ጨርሷል ... እኛስ?

እንደሚታቀው አብዛኛዎቹ የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አባላት በግንቦት 1997 ምርጫ ንቁ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ የንቅናቄውም ከፍተኛ አመራር እንዲሁም በ1997 ምርጫ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፈ ነው፤ ስለምርጫው በቂ እውቀት አለው፡፡ አመራሩ የምርጫ 97 ልምድን አበጥሮ መርምሯል፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህ ምርምር በመነሳት አሁን አገራችን በምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ ምርጫ የሚኖረውን ትርጉም በግልጽ አስቀምጧል፡፡ «ምርጫ የሕዝብን ድመፅ ህገወጥ በሆነ መንገድ ቀምቶ በጠመንጃ ኃይል ዘረኛና ዘራፊ አገዛዙን የዘረጋውን አምባገነናዊ የወያኔ አገዛዝ ህጋዊ እውቅና መስጠትና ማጠናከር ይሆናል» ብሏል፡፡ «በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት የሚቻለው የሥርዓቱን ግፈኛ ገጽታ ለመሸፈን ወያኔ በሚጠራው ምርጫ አይደለም፡፡ እንዲያውም በአገራችን እውነተኛ ምርጫ ማድረግ የሚቻለው ወያኔ ከሥልጣን ተወግዶ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ባቀፈ የዲሞክራሲ የሽግግር ሂደት ማለፍ ስትችል ብቻ መሆኑን» ግንቦት ሰባት በማያሻማ ቋንቋ ገልጧል፡፡ ግንቦት 7 ይህንን አይነቱን የሽግግር ሂደት በአገራችን ለማስጀመር ዲሞክራሲያዊ ራዕይ አንግቦ፣ ማኛቸውንም የትግል ስልት በመጠቀም ከሕዝብና ለዴሞክራሲያ ሂደቱ መጀመር ቅድሚያ ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር በመደጋገፍ መራራውን ትግል ጀምሯል፡፡ ያም ሆኖ የ2002 የወያኔ የምርጫ ቲያትር ጊዜ እየደረሰ ነው፡፡ ይህን ተንተርሶ የተጠበቁና የማይቀሩ የማደናገሪያ እርምጃዎቹን ወያኔ መውሰድ ጀምሯል፡፡ ሕዝቡና የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ እንዲሁም በሃገራችን ያሉት የዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ አባላት ለዚህ የወያኔ እስክስታ የሚመልሱት መልስ ሕዝባዊ ውይይት ስለሚያስፈልገው የንቅናቄያችንን አቋም ለመግለጽ ይህንን ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

### 2. ምን ዓይነት ምርጫ፡ ነፃ ወይስ የሴራ ምርጫ?

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማለቅ በኋላ በታዳጊው ዓለም ጎራ ያሉ ሁሉም ዓይነት መንግሥታት ምርጫን የሥልጣናቸው ሕጋዊና ሞራላዊ መሠረት ለማድረግ እየሞከሩ ነው። ይህ የምርጫ ሙከራ እንደተጀመረም በምርጫ ወደ ሥልጣን የወጡትን መንግሥታት ከዚህ በፊት ከነበሩት ፈላጭ ቆራጭ የነገሥታት፣ የወታደራዊና የአንድ ፓርቲ አገዛዞች ጋር በማነጻጸር የተሻሉ ጅምሮች ናቸው የሚሉ እምነቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረው ነበር። ምናልባትም እነዚህ ምርጫዎች በሂደት ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመሄጃ በር ይከፍቱ ይሆናል በሚል መላምት በደፈናው እንደ መሻሻል የታዩበት ሁኔታ ተከስቶ ነበር። ከ 20 ዓመታት ልምድ በኋላ የታየው ተጨባጭ ሁኔታ ግን ቀደም ተብሎ ተይዞ የነበረውን ተስፋ ያደበዘዘ ሆኗል፡፡ እርግጥ ነው ጥቂት ምርጫዎች እውነተኛ የሆነ የዴሞክራሲ ሂደትና ግንባታ በጥቂት ሃገሮች ላይ እንዲጀመር አስችለዋል፡፡ ብዙዎቹ ምርጫዎች ግን ከቀድሞው ባልተሻለ ሁኔታ የፖለቲካ ጭቆና፡ የኢኮኖሚ ገፈፋና የጥቂት አምባገነኖች ግፈኛ አገዛዝ የመከለያ ሽፋን ሆነው አርፈውታል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዓለማችን ውስጥ አራትና አምስት አመት እየጠበቁና አስመሳይ ምርጫቸውን እያካሄዱ የአንድ ፓርቲ ወይም የአንድ ግለሰብ አገዛዛቸውን በምርጫ ስም የህጋዊነትና የሞራል ልባስ ለማለበስ ሙከራ የሚያደርጉ አምባገኖነች ቁጥራቸው እየተበራከተ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች በሥራ ላይ እየዋለ ያለው በማጭበርበር ሴራ ላይ የተመሰረተ ምርጫ ውጤቱ በጥቂቶች የበላይነት በዘር የተደራጀ የፖለቲካ ሥርዓት ማጠናከር ሆኗል፡፡ ከአገሪቱ ሕዝብ 5 በመቶ የማይበልጠውን የትግራይ ህዝብ «በትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭነቴ እወክላለሁ» የሚል ነገር ግን የእዚህ ውክልና እንዳለው ግን ምንም አይነት ዴሞክራሲያዊ ማረጋገጫ የሌለው ጠባብ ቡድን፣ ዘረኛ አገዛዙን በመላው አገሪቱ ህዝብ ላይ የሚጭንበት የማጭበርበሪያ ስልት ምርጫ ሆኗል፡፡

ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው ሁለት ዓይነት የምርጫ ልምዶች በመነሳት በአሁኑ ጊዜ የዲሞክራሲና የምርጫ ሂደት የሚከታቱሉና የሚመረምሩ ጋዜጠኞችና ተመራማሪዎች ምርጫን በሁለት ቦታ ከፍለው እንዲያዩ ተገደዋል።

በአንድ በኩል ምርጫ የፖለቲካ ቡድኖች ትርጉም ባለው መልክ ተወዳድረው የሕዝብ ውክልና እና ተጠያቂነት ያለው መንግሥት መመሥረቻ ሁኗል። በዚህም ሂደት አገራት ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን እየገነቡና እያጠናከሩ፣ በማኅበረሰባቸው ውስጥ ዲሞክራሲ ባህልና አሰራር እንዲጎለብት፣ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ እሴቶች ከፍተኛ ክብር እንዲሰጥ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሃገሮች ውስጥ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ እድገት መሰላል፤ የሰላምና የመረጋገት ዋስትና፤ የማኅበራዊ ችግሮች ማቃለያ እና የሰብአዊ ክብርና መብት ማስጠበቂያ መሣሪያ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ አምባገነኖች ምርጫን የሚፈልጉት ሥልጣናቸውን ሞራላዊና ህጋዊ ለማድረግ ብቻ እንደሆነ ግልጽ ሆኗል፡፡ እነዚህ አምባገነኖች በአንድ በኩል የመንግስት ሥልጣን መያዝ ያለበት በሕዝብ ነጻ ፈቃድ ላይ በተመሠረተ ምርጫ ነው የሚለው እሳቤ፣ የዘመኑ የሰው ልጆች ሁሉ ገዢ እምነት መሆኑን ተረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ገንዘቡና ጉልበቱ ያላቸው በርካታ የዓለም አገሮች ለዴሞክራሲና ለምርጫ ትልቅ ቦታ እየሰጡ መምጣቸው ገብቷቸዋል፡፡ ይህ እውነታ አምባገነኖች እንደቀድሞው «የምን ምርጫ! የምን ዴሞክራሲ!» ብለው እየደነፉ መቀጠል የማይችሉበትን ሁኔታ እንደፈጠረ ያውቃሉ፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ድሃና የመንግሥታዊ በጀታቸው ከፍተኛ መጠን ያለው ድርሻ በምዕራብ መንግሥታት እርጥባን የሚሟሉላቸው፤ የራሳቸው ኢኮኖሚያዊ ሉዓላዊነት የሌላቸው አገራት ገዥዎች እንደ ቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ለብድርና ለእርዳታ የሚሄዱበት ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ሳይወዱ በግድ የዴሞክራሲ ጨዋታ ውስጥ እንዲገቡ ተገደዋል፡፡ የዓለማችን የደሃ አገራት አምባገነን መሪዎች የዴሞክራሲና የምርጫ ጨዋታ ውስጥ ሳይገቡ ከምዕራባውያን የሚያገኙት እርዳታ ቀጥ ሊል እንደሚችል ሰለሚውቁ ስለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሃሰት መዝሙራቸውን ለመዘመር ተገደዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ቢያደርጉ አምባገነናዊና በሙስና የተበከለ የገዥነት ታሪካቸው በቀላሉ በምርጫ ተሸንፈው ከሥልጣን እንዲነቀሉ የሚያደርጋቸው መሆኑን ይረዳሉ፡፡ ከእዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ውጤቱን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት፤ እነሱን ከሥልጣን መንቀል ቀርቶ ሥልጣናቸውን ሊገድብ እንኳን በማይችል መንገድ ውጤቱ አስቀድሞ የታወቀ የይስሙላ ምርጫ ማድረግ ከሁሉ የተሻላ አማራጭ አካሄድ ሆኖ አግኝተውታል፤ ዝርዝር አሠራሩንም ሰልጥነውበታል፡፡ እንዲህ አይነቱ የማስመሰልና የማጭበርበሪያ ምርጫ የሚያደርጉ የዓለማችን አምባገነን ኃይሎች በርካታ ናቸው። ይህም ግንዛቤ የዓለማችንን የዲሞክራሲ ሂደት በአትኩሮት ከሚመለከቱት ታዛቢዎች አልፎ በአምባገነኖች ሥር ያሉ ሕዝቦች ሁሉ የተረዱት ሃቅ ሆኗል፡፡ ይህ እውነታ ደግሞ አምባገነኖች ምርጫን እንዳሻቸው መቆጣጠር የሚችሉበት አቅማቸውና ብልጣብልጥነታቸው በሙሉ ተሟጦ ማለቅ መጀመሩን ያሳያል።

በይስሙላ ምርጫ የአገሩን ሕዝብና ዓለም-ዓቀፍ ማኅበረሰብን ማጭበርበር እንደማይችሉ የተረዱ አንዳንድ አምባገነኖች የማፈግፈግ እርምጃን ሲመርጡ (ለምሳሌ ኬንያና ዚምባብዌ) ሌሎቹ ግን ባገጠጠ መልኩ ሕዝብን የማፈንና የማስፈራራት እርምጃዎችንና ምርጫንም ከበፊቱ በባሰ በማጥበብ መሄድን መርጠዋል። (ለዚህ አይነቱ እብሪት የመለስ-በረከት አገዛዝ ሁነኛ ምሳሌ ሲሆን ግብፅና ምናልባትም ኢራን በሰሞኑ አካሄዳቸው ከቀጠሉ ተከታይ ምሳሌች ሊባሉ ይችላሉ)።

ወያኔ ምርጫን ምን ያህል በሙሉ ቁጥጥሩ ውስጥ እንዳስገባውና በማስመሰያነት እንደሚጠቀምበት ለመገንዘብ በ2000 ዓ.ም የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫዎች የተጫወተውን ቲያትር መመርመር በቂ ነው። በአዲስ አበባ ውስጥ ከሁለት ዓመታት በፊት አንድ ተመራጭ ማስመረጥ ያቃተው ወያኔ በዚህ ምርጫ «የከተማው አቸናፊ ተመራጮች ሙሉ በሙሉ የእኔ እጩዎች ናቸው» አለ። ይህ በተዓምር ደረጃ ሊታይ የሚገባው ጉድ የሚያመለክተው የመለስ-በረከት ቡድን የሕዝብን ልብ የመቀየር ቀዶ ጥገና እውቀቱ እጅግ የረቀቀ፣ በዓለማችን ተሰምቶና ታይቶ ከማይታወቅ ደረጃ መድረሱን ነው። በተባባሰ ግድያ፣ እስራት፣ አፈናና ዘረፋ የሶስት አመት ግዜ፣ ወያኔ በአዲስ አባባ ውስጥ ከዜሮ ወንበር ወደ ሁሉንም ወንበር ባለቤትነት የተሸጋገረበት ሁኔታ የሚያረጋግጠው ያለ ዕውነተኛ የውድድር ቅድመ ሁኔታዎች ምርጫ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ነው፡፡

### 2.1 የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ?

ከላይ እንደጠቀስነው ከ20 ዓመታት የምርጫ ማጭበረበር ልምዶች በኋላ አምባገነኖች ለክተው በሰጡን መጠን ወንበር ተቀብለን ይህን ድርጊታችንን የዲሞክራሲ ሂደት ነው ብለን እርስ በርሳችን መከራከር የማንችልበት ህዝባችንንም ማጭበርበር ከማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በተለይ በ97 ምርጫ የድል ተራራ አፋፍ ላይ ደርሶ በወያኔ አጋዚ ጦር አሽቆልቁሎ እንዲመለስ የተደረገን የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ወያኔ ሥልጣኑን ቅንጣት እንኳን በማትነካው መልኩ በሰጠን ወንበር ውስጥ ለመቀመጥ ብቻ ወያኔን በምርጫ ተብዬ ቀልድ ማጀብ የሕዝብ ወገኖች ለሆኑ ሁሉ በጭራሽ የማይመጥናቸው ተግባር ነው ብለን እናምናለን።

የሕዝብን ስሜት የሚያስተጋቡ ተቃዋሚዎች ከአሁኑ ፈጥነው ማድረግ ያለባቸው ምርጫ ለአምባገነኖች የህጋዊነትነትና የሞራል ሽፋን መስጫ ሳይሆን እውነተኛ የሕዝብ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት፣ ይህ ፍላጎት ብቻ የአገርን፣ የመንግሥትንና የዜጎችን እጣ የሚወሰን ልዕልና ያለው የሚሆንበትን ሁኔታ እንዴት እንፈጠራለን ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ነው፡፡ ባጭሩ እነመለስ በተጭበረበረ ምርጫ ዘረኛ፣ አምባገነናዊና የዘረፋ ስርአታቸውን የማስቀጠል ሥራ እየሰሩ መሆኑን በመረዳት መጪው ምርጫ በተጻራረው የሕዘብ ፍላጎት በነጻ የተገለጸበት ምርጫ እንዲሆን ለማድርግ አቅዶ መንቀሳቀስ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የቅንጅት መሪዎች እንዳደረጉት ድምጹን የተዘረፈውም ህዝብ ድጋፉን በደሙ ሳይቀር እንደሰጠበት፣ ምርጫ የአምባገነንነት መጋረጃ ሳይሆን በእውነት ለመንግሥት ሥልጣን መወዳደሪያ እንዲሆን የሚያስፈልጉትን አገራዊ ቅድመ ሁኔታዎች ዘርዝሮ፣ ለእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች የኢትዮጵያን ሕዝብና የወያኔ አፈና አላነቃንቅ ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ በማስተባበር መታገል ነው፡፡ ይህን ትግል በውጭ በሚገኘውና ትልቅ አስዋጽኦ ማደረግ ወደሚችለው ኢትዮጵያዊም ማድረስ ይገባል፡፡ ሃቀኛ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖር መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በአገርችንና በአካባቢያችን ጉዳይ ያገባናል ለሚሉ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ብሄራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችን ይነካል ብለው ለሚያስቡ የዲፕሎማሲያዊ ማኅበረሰባትና ለራሱም ለወያኔ ማቅረብ ያስፈልጋል። በዚህ በኩል እስካሁን መኢአድ ያደረገው በአርአያነቱ የሚጠቀስ ነው። (ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## ዘረኛውን አገዛዝ አስወግደን ፍትሃዊ እና ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመንገንባት ሂደት ልንጀምር ይገባል

ወያኔ በተደጋጋሚ የብሔረሰቦችን መብት ስለማስከበሩ እንደሚያወራ ይታወቃል። እውነታው ግን፣ የብሔረሰቦች መብት ለወያኔ ዘረኛነቱን ለመሸፈን ከሚጠቀምባቸው ጭንብሎች አንዱ ከመሆኑ ባሻገር በተግባር ያሳየው ነገር አይደለም።

በመሰረቱ ዘረኛ የሆነና ከአንድ መንደር እና ቤተሰብ የመጡ ሰዎች በአገሪቱ ላይ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ የበላይነት እንዲኖራቸው ተግቶ የሚሰራ ቡድን የብሔረሰቦችን መብት በእውነት ሊያስከብር አይችልም። ሊያደርጋቸው የሚችላቸው ብቸኛ ነገሮች ህዝቡን ለማታለል የተዘጋጁ ተውኔቶችን ማካሄድ ነው። የብሔር ብሔረሰቦች ቀን መሰየም፤ የብሔር ብሔረሰቦች አደባባይ እያለ ስም ማውጣት እና የመሳሰሉት ተግባራት ለዚህ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ። ወደ ውስጥ ጠለቅ ብለን ስንመለከት ግን እነዚህ አደባባይ የተሰየመላቸው እና ቀን የተሰጣቸው ብሔር ብሔረሰቦች፤ እየተገፉ፣ እየተረገጡ፣ እና እየተዘረፉ ይገኛሉ።

በአንዲት አገር የብሄረሰቦች መብት መከበር እራሱን ከሚገልጥባቸው መንገዶች አንዱ ፍትሃዊ በሆነ የስልጣን ክፍፍል ነው። ፍትሃዊ ስንል ግዴታ ከህዝቦች ቁጥር ጋር የተያያዘ ኮታ የሚያሟላ ማለታችን አይደለም። ይልቁንስ በብቃት ላይ የተመሰረተ እና ከማንኛውም ብሔረሰብ የወጣ እና ብቃቱን ያስመሰከረ ዜጋ ሊካፈልበት የሚችል ሁኔታ ማለታችን ነው።

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የስልጣን ክፍፍል ግን፣ ብቃትን ሳይሆን አይን ያወጣን ዘረኛ አሰራር የሚከተል ነው። በጦሩ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እንደ ምሳሌ ብንጠቅስ፤ ከስልሳ ቁልፍ የስልጣን ቦታዎች ውስጥ ሃምሳ ስድስቱ ከአንድ ዘውግ፣ ማለትም ከትግራይ የወጡ ሲሆኑ፤ በአገሪቱ ውስጥ በህዝብ ብዛት ታላቁን ቁጥር ከሚይዘው ከኦሮሞ ህዝብ የወጣ ግለሰብ አንድም መቀመጫ የለውም። ይህ ታዲያ በማንኛውም መመዘኛ ቢታይ ትግራውያን ብቻ በጦር ስራ ብቁ ሆነው፤ ከኦሮሞ ህዝብ ግን ብቁ የሆነ አንድም ሊገኝ አልቻለም ወደሚለው ድምዳሜ ሊወስድ አይችልም። ጉዳዩ ግልጽ ነው፦ ያም በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ዘረኛ መሆኑ ነው።

እንግዲህ የወያኔ ዘረኛነት ከኢትዮጵያውያን አልፎ ለተቀረው አለም ግልጽ ወደሆነበት ደረጃ ደርሷል። የተወሰኑ አለም አቀፍ የምርምር ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የዘር ቅራኔ ወደከፋ ችግር ሊወስድ እንደሚችል በመናገር መንግስታቶቻቸው በወያኔ ላይ የሚከተሉትን ፖሊሲ እንዲመረምሩ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል። በዚህ ሳምንት ፍሪደም ሃውስ የተባለው አንጋፋ አለም አቀፍ ተቋም የወያኔ አገዛዝ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የዘር አድሎ እንደሚፈጽም እና ከትግራይ ለሆኑ ሰዎች እንደሚያደላ ተናግሯል። በሌሎች ብሔረሰቦች ላይም በሰፊው አድሎ እንደሚፈጸም መስክሯል።

የዚህ እንድምታ እንግዲህ ግልጽ ነው፦ ወያኔ በኢትዮጵያ የመንግስትን ስልጣን በሃይል ተቆጣጥሮ እስከቆየ ድረስ ሰላም እና መረጋጋት ይኖራል የሚል ዋስትና የለም። ውስጥ ውስጡን የሚፈላው ቅራኔ በማንኛውም ጊዜ ሊገነፍል እና ለከፋ አደጋ ሊዳርገን ይችላል። በኢትዮጵያ መረጋጋት ተጠቃሚዎችን ነን የሚሉ የውጭ መንግስታት ለራሳቸው ችግር ይጨነቁ። በአገራችን ጸብ እና አለመረጋጋት ቢነሳ ዋና ተጎጂዎቹ የምንሆነው እኛ ነን።

ስለዚህም ወደዛ ከመድረሳችን በፊት ዘረኛውን አገዛዝ አስወግደን ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት ተከብሮ እና በአገሩ ኮርቶ የሚኖርበትን ፍትሃዊ እና ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመንገንባት ሂደት ልንጀምር ይገባል። ይህ የሁላችንንም ጥንካሬ፣ ፈቃደኝነት እና ትብብር የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

## የወያኔ ጦር የወታደሮች ፍልሰት ችግር እንዳለበት ታወቀ

የወያኔ ጦር ከፍተኛ የሆነ የወታደሮች ፍልሰት ችግር እንዳለበት የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከኢትዮጵያ በላከው ዘገባ አስታውቋል።

ዘጋቢው ከሰሜን ኢትዮጵያ ባስተላለፈው መረጃ፣ በሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ በጠገዴ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ተሰማርቶ የነበረው የ4ኛ ሻለቃ ልዩ ሃይል በደረሰበት የወታደሮች ፍልሰት በመዳከሙ አገዛዙ በአዲስ ምሩቆች ሊሞላው ተገዷል። አብዛኞቹ ወታደሮች በክህደት እንደሚለቁ የታወቀ ሲሆን፤ የተቀሩት በምግባረ ብልሹነት ሰበብ እንደሚባረሩም መረጃው አስረድቷል። የወያኔ አገዛዝ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ይደግፋሉ ብሎ የሚጠረጥራቸውን ወይም ለዘር አድሎ አሰራሩ ምቹ ሆነው ያልተገኙትን የጦር አባላት በምግባረ ብልሹነት እያሳበበ የማባረር የቆየ ልምድ እንዳለው ይታወቃል።

የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር ወደ ሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ማጓጓዝ መጀመሩን ማክሰኞ እለት ዘግበናል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ አገዛዙ ልዩ ሃይል የሚባል አዲስ ሰልጣኝ ጦር አስመርቆ ከግንቦት 22 ቀን 2002 አመተ ምህረት ጀምሮ በተለያዩ ሰሜናዊ የአገሪቱ ወረዳዎች እያጓጓዘ መሆኑ ታውቋል። ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ አዲስ ምሩቃንም በጠገዴ የተዳከመውን የ4ኛ ሻለቃ ልዩ ሃይል እንዲያጠናክሩ መመደባቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

በጦሩ ውስጥ ከሚካሄደው የዘር አድሎ እና ሌላም ኢ-ፍትሃዊ አሰራር የተነሳ በርካታ አባላቱ በየጊዜው እንደሚኮበልሉ ይታወቃል። እስካሁን የታየው ፍልሰት ግን በጦሩ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚንጸባረቀውን ቅራኔ እንደማይገልጽ እና እድሉን ቢያገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች እንደሚከዱ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ሰዎች ይናገራሉ።

## በቅርቡ በኬንያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተሾመች ግለሰብ የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነች ተባለ

በኬንያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የኢሚግሬሽን ካውንስለር ሆና በቅርቡ የተመደበችው ግለሰብ ለስራው የሚያስፈልገውን ብቃት የሌላት እና የወያኔ አገዛዝ ዘረኛ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነች ሲሉ የኤምባሲው ምንጮች ስሞታ አሰምተዋል።

ለግንቦት 7 ድምጽ ከስፍራው የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ አለም ተክሉ የተባለችው ግለሰብ የወያኔ የቀድሞ ታጋይ ስትሆን፣ የተማረችው እስከ ሶስተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነው። ኤምባሲው ኬንያን ጨምሮ ለታንዛኒያ፣ ማላዊ እና ማዳጋስካር አገልግሎት የሚሰጥ እንደመሆኑ ከፍተኛ ሃላፊነት ያለበት ነው። አለም ተክሉ የተመደበችበት ሃላፊነት ከነዚህ አራት አገራት ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ ቪዛ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር የሚያገናኛት ቢሆንም፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር እንደማትችል ምንጮቻችን ገልጸዋል።

አለም ተክሉ ለዚህ ስራ በየወሩ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ የአሜሪካን ዶላር እንደሚከፈላት እና ይህም ከሌሎች ተነፃፃሪ ሃላፊነት ካላቸው የኤምባሲ ሰራተኞች ክፍያ ጋር ሲወዳደር እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ታውቋል። እሷ በኤምባሲው በተመደበችበት ሰሞን፣ ሁለት ኦሮሞ የሆኑ የኤምባሲው ነባር ሰራተኞች ባልታወቀ ምክንያት ከስራቸው ተባረዋል። እነዚህ ግለሰቦች ለነበራቸው ሃላፊነት ብቃት እንዳላቸው አስመስክረው የተቀጠሩ ሲሆን፤ የአንደኛው የወር ደሞዝ 465 የአሜሪካ ዶላር፣ የሌላኛው ደግሞ 410 የአሜሪካ ዶላር ነበር።

## ፍሪደም ሃውስ የተባለው ተቋም የወያኔ አገዛዝ የዘር አድሎ ይፈጽማል፤ በኢትዮጵያ ያለው አፈናም ከቀደመው አመት የከፋ ሆኗል አለ

ፍሬደም ሃውስ የተባለው አንጋፋ አለም አቀፍ የነፃነት ተሟጋች ድርጅት ሰሞኑን ባወጣው አመታዊ ሪፖርት የወያኔ አገዛዝ የዘር አድሎን በሰፊው እንደሚፈጽም፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሁኔታ ከቀደመው አመት የከፋ መሆኑን ገልጿል።

ተቋሙ የወያኔ አገዛዝ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የዘር አድሎ እንደሚፈጽም እና ከትግራይ ለሆኑ ሰዎች እንደሚያደላ ተናግሯል። በሌሎች ብሔረሰቦች ላይም በሰፊው አድሎ እንደሚፈጸም መስክሯል።

ፍሪደም ሃውስ የወያኔ አገዛዝ በሲቪል ተቋማት ላይ የሚያካሄደውን አፈና፣ ጸረ-ሽብር ተብዬውን ህግ፤ እንዲሁም በተቃዋሚዎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እንደምክንያት በመጥቀስ በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ነፃነት ሁኔታ ከቀደመው አመት የከፋ መሆኑን ገልጿል። የወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ እስር፤ አገዛዙ የሚጠቀምባቸው የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ከሞላ ጎደል የመረጃ ሜዳውን መቆጣጠራቸው፤ የብዙ ነፃ ሚድያ ድርጅቶች መዘጋት እና በተቀሩት ላይ የሚደርሰው አፈና በሪፖርቱ ውስጥ ተጠቅሰዋል።

ፍሪደም ሃውስ በዚሁ ሪፖርቱ፣ በኢትዮጵያ የትምህርት ወይም አካዳሚክ ነፃነት የተገታ እንደሆነ ጠቅሷል። የወያኔ አገዛዝ ትምህርት ቤቶች ለተቃዋሚዎች ቅርብ ናቸው በሚል እንደሚከስ እና በቅርብ እንደሚቆጣጠራቸው ተናግሯል።

ተቋሙ ኢትዮጵያን በከፊል ነፃ ከሚባሉ አገሮች ቡድን ውስጥ የመደበ ቢሆንም፤ ይህ ሪፖርቱ የተጠናከረው ግን በርካቶች ኢትዮጵያን የአንድ ፓርቲ አገር ብለው የፈረጁበት የግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ከመካሄዱ በፊት ነበር።

### መድረክ ፓርቲ የምርጫ ቦርድን ውሳኔ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መድረክ አቤቱታውን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ የወሰነው ቦርዱ ውሳኔውን ያካሄደበት መንገድ ትክክለኛ ባለመሆኑ ነው ሲሉ ዶ/ር በየነ ለሬውተርስ ነግረዋል። ፍርድ ቤቶችም በወያኔ አገዛዝ ሙሉ ቁጥጥር ስር እንዳሉ የሚታወቅ ሲሆን፤ በተለይም በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ከማስተላለፋቸው በፊት ዳኞች ከባለስልጣናት ትእዛዝ እንደሚቀበሉ ይታወቃል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org